## ቁጭ ብለን ተቀምጠን

አቤት እንዴት እንደሚሄድ
          አንደሚነጉድ ፀሃዩ
እያየሁት ሳላየው
          እያዩ እየተያዩ።

ቁጭ ብለን ተቀምጠን
          ተቀምጠን ቁጭ ብለን
ንፋስ ብርድ እንዳያገኘው
          ድንጋዩን እናሞቃለን።

ደስ አዴልም ግን ሃሳባችን
          የአንጀታችን ርህራሄ፣
ከሰው አልፈን ለግዑዙ
          ለድንጋይ ለንሰጥ መፍትሄ!
እንዴ! እንዴት ላናስብ ለድንጋይ
          ለታላቁ ወንድማችን
እንዳውም ንቀት ነው እኮ
          እላዩ መቀመጣችን።

ምንም ቁመናችን ቢያምር
          ቢማርክ አካሄዳችን
ሁለት እግሮች ያሉን
     መልከ መልካም ድንጋዮች ነን።
እናም እስቲ እንቀመጥ፣
        ተቀምጠን ተድበልብለን
እንደማምቀው ሰፈፉን፣
        የድንጋይ ውበት እንሁን።

አይችሉህም አበበ እሸቴ<br>*ለኞ ግንቦት 9/2002 ዓ.ም.*

<u>**ሳልም**</u>

እሺ፣
ጠረጴዛው ላይ ቁጭ ብዬ ፣ ስንቦጃቦጅ ስጠረጵዝ
ቡዝዝ ብለው አይኖቼ ፣ ሁለመናዬ በቁም ሲፈዝ
በዝምታዬ አናት ላይ ፣ በብዥታው ውዥቀት መሃል
ውልብ አለች አበባዋ ፣ እንደ ህልም አለም ባለሟል።

የህልም ዓለም ባለሟል ፣ ሁሉ የተሳካለት
ያሻውን ከቶ ‘ማያጣ ፣ የሚኖር እንዳ’ማረበት
እሱን መስላ ታየችኝ ፣ የህልሜ ውስጥ ህልም አበባ
ለህይወቴ ህይወት ስትሰጥ ፣ እኔነቴን በሷ ክባ።

አይችሉህም አበበ እሸቴ

<u>ማንበብና መፃፍ</u>

ታላቅ ትልቅ ሚስጥር፣ የህይወት ሰዋሰው
ማንበብ መፃፍ ላይ ነው፣ የተመረኮዘው፡፡

መፃፍ ብቻ ሳይሆን፣ ማንበብ ታላቅ ነገር
ያብሮነት ሰንሰለት
-የህብረትን መረብ
እሱ ነው የ’ሚያስር፡፡

*ማንበብና መፀፍ-እንዲህ ነው እያለ ሰው ሁሉ ሲነግረኝ*
*እኔስ መፃፍ እንጂ፣ማንበቡ ቸገረኝ፡፡*

አይችሉህም አበበ እሸቴ

ማክሰኞ ነሐሴ 11/2002 ዓ.ም.
ጠዋት 4፡20

---

ይሄን ትመስላለች፣ ህይወት በደፈናው፣ በግርድፍ ግርድፉ
እየተገናኙ እየተላለፉ፡፡

ያየ ያየ መስሎት እያየ ሳያየው
የህይወትን መንገድ በግርድፍ ዘለለው፡፡

አይችሉህም አበበ እሸቴ

ሐሙስ ነሐሴ 13/2002 ዓ.ም.
ጠዋት 5፡30

**ውስጠት**

ግን ውስጠት ምንድነው ከውስጥ ካልወጣ
ካልታየ ላገሩ ቤት ደፍቶ ካልመታ
ካልተተረጎመ ህይወት ካልዘራበት
ውስጠት ጨለማ ነው የጋን ውስጥ መብራት፡፡

አይችሉህም አበበ እሸቴ

ሐሙስ ነሐሴ 13/2002 ዓ.ም.
ጠዋት 5፡35

የዘላቂነት ዝልቀቱ የት እንደሚያዘልቅ እስካየው
ቀኔን እጠብቃለው፡፡

አይችሉህም አበበ እሸቴ

ቅዳሜ፡ መስከረም 29/2002

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by** Meskot**. You may contact Aychiluhim Abebe  for comments at** aychye@yahoo.com**.***